# 441

የእንግሊዝና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ማኅበር ፡ ጥቅምት ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሰኞ ፡ ስለ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ክብር ፡ ከማታው ፡ ፲፪ ፡ እስከ ፡ ፪ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ባደረገው ፡ የሬሴፕሲዮን ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ተገኙ ። በግብዣውም ፡ ላይ ፡ የማኅበሩ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ለተናገሩት ፡ ቃል ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠው ፡ መልስ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

ክቡር ፡ ሆይ ።

የእንግሊዝና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ማኅበር ፡ ማኅበረተኞች ።

ከእንግሊዝና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ማኅበር ፡ አባሎች ፡ ጋራ ፡ ወደዚህ ፡ በመጣሁበት ፡ ጊዜ ፡ ለመገናኘት ፡ አጋጣሚ ፡ ስላገኘሁ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ።

አገሬ ፡ የጎዘን ፡ ጥላ ፡ ሸፍኗት ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ የተመሠረተው ፡ ይህ ፡ ማኅበር ፡ ከዚያ ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ባለፉት ፡ በክፉዎቹ ፡ አሁንም ፡ በመልካሞቹ ፡ ቀኖች ፡ ለእኔና ፡ ላገሬ ፡ በታማኝነትና ፡ በወዳጅነት ፡ ሲሠራ ፡ እንደ፡ኖረ ፡ ግልጥ ፡ ነው ። በንግግርዎ ፡ አስተካክለው ፡ እንደ ፡ ገለጡት ፡ ይህ ፡ የዛሬ ፡ ስብሰባ ፡ በእውነት ፡ የወዳጅነት ፡ ስብሰባ ፡ ሊባል ፡ የሚቻል ፡ ነው ። ላገሬ ፡ ያላቸው ፡ መልካም ፡ አስተያየት ፡ ፍቱን ፡ መሆኑን ፡ የገለጡትን ፡ የዚህን ፡ ማኅበር ፡ አባሎች ፡ ለማግኘት ፡ በመቻሌ ፡ ወደዚህ ፡ ከመጣሁ ፡ ጀምሮ ፡ በየቀኑ ፡ ላደረብኝ ፡ መልካም ፡ ስሜት ፡ ታላቅ ፡ ብርታት ፡ ሰጥቶታል ። ዛሬ ፡ በመካከላችሁ ፡ እንድገኝ ፡ ላደረጋችሁልኝ ፡ ጥሪና ፤ ሊሰጥበት ፡ የሚገባውን ፡ ጊዜ ፡ በመጠበቅ ፡ ያቈያችሁትን ፡ ይህን ፡ ታሪካዊ ፡ ጽሑፍ ፡ ስላበረከታችሁልኝ ፡ እርስዎን ፡ የማኅበሩን ፡ ፕሬዚዳትንና ፡ አባሎቹን ፡ በሙሉ ፡ እጅግ ፡ አመሰግናቸዋለሁ ። ይህን ፡ የመሰለ ፡ ስጦታ ፡ ለማበርከት ፡ ከመረጣችሁት ፡ ካሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የተሻለ ፡ ሊገኝለት ፡ አይችልም ። ይህም ፡ መታሰቢያችሁ ፡ የተከበረ ፡ ቦታውን ፡ ይዞ ፡ ይኖራል ።

ስለ ፡ መልካም ፡ ስጦታችሁና ፡ በንግግርዎ ፡ እንደ ፡ ገለጡት ፡ የእንግሊዝና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ማኅበር ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ላሳየው ፡ ወዳጅ



ነትና ፡ ላደረገልኝ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ አቀባበል ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ ምስጋና ፡ አቀርብላችኋለሁ ።

---

# 442

የእንግሊዝ ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር ፡ ሚስተር ፡ አንቶኒ ፡ ኤድን ፡ ጥቅምት ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት ፡ ክብር ፡ ባደረጉት፡ የእራት፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ተገኝተው ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስትሩ ፡ ንግግር ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተነገረው ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

ሰር ፡ አንቶኒ ፡ ኤድን ።

እኔ ፡ ራሴ ፡ ከታገልሁበትና ፡ ከብዙ ፡ ፈተና ፡ ካለፍሁበት ፡ ጉዳይ ፡ ከኮሌክቲብ ፡ ሴክዩሪቲ ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ ጋራ ፡ ስምዎ ፡ በታሪክ ፡ ተያይዞ ፡ የሚገኘው ፡ የተከበሩት ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር ፡ ባደረጉልኝ ፡ ግብዣ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ።

ታላቁን ፡ ሥራዎን ፡ ለመሥራት ፡ የጀመሩት ፡ ለመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትርነትን ፡ ከተቀበሉበት ፡ ከዛሬ ፡ ሐያ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ነው ። ይህን ፡ ሥራ ፡ በመቀበልዎ ፡ የኮሌክቲብ ፡ ሴክዩሪቲን ፡ ከፍተኛ ፡ አሳብ ፡ በፍጹም ፡ ደጋፊ ፡ ሆነው ፡ በነዚያ ፡ በገጠሙዎት ፡ ታሪካዊና ፡ አስቸጋሪ ፡ ዘመናት ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ ለተጣለብዎ ፡ አደራ ፡ ታማኝነትዎን ፡ አላጓደሉም ።

የመንግሥታት ፡ ማኅበር፡ በታሪክ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የሆነውን ፡ የጎብረት ፡ ጭቆና ፡ እንዲወስን ፡ ለማድረግ ፡ የረዱንንና ፡ ያሳዩትን ፡ መሪነት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከውለታ ፡ ጋራ ፡ ታስታውሰዋለች ።

በኮሌክቲብ ፡ ሴክዩሪቲ ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ አፈጻጸም ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሰናክልና ፡ ችግር ፡ ቢገጥምዎ ፡ ለነዚህ ፡ መሪ ፡ አሳቦች ፡ ጽኑ ፡ ታማኝ፡ ሆነው፡ መገኘትዎን ፡ የነዚያው ፡ ዘመኖች ፡ ታሪክ ፡ ይመሰክርልዎታል ።

በአገራችን ፡ በእርስዎም ፡ በኔም ፡ መሪነት ፡ የተፈጸመው ፡ ዐይነተኛ ፡ የዚያ ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ እውነተኛነት ፡ ሊገለጽ ፡ እንደ ፡ ተቻለ ፡ አምናለሁ ።

በዚህ ፡ ረገድ፡ ለተገኘው ፡ መልካም ፡ ፍጻሜና ፡ እጅግ ፡ ከፍ፡ ላለው ፡ አሳብ ፡ የጋራ ፡ በሆነው ፡ ተጋድሎ ፡ ለተሳሰሩት ፡ ለሁለቱ፡ አገሮቻችን ፡ ወዳጅነት ፡ ጽናት ፡ ጽዋዬን ፡ አነሣለሁ ።

# 443

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጥቅምት ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሎንዶን ፡ በቢቢሲ ፡ የራዲዮ ፡ ጣቢያ ፡ በቴሌቭዥዮን ፡ ታይተው ፡ ያደረጉት ፡ ንግግር ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ በደስታ ፡ ተመልሰን ፡ በዛሬው ፡ ቀን ፡ ከወዳጆቻችን ፡ ከታላቂቱ፡ ብሪታንያ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ከሎንዶን ፡ ንግግር ፡ ልናደርግላችሁ ፡ በመቻላችን ፡ ደስ ፡ ብሎናል ።

በእንግሊዝና ፡ በኢትዮጵያ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የቈየ ፡ መሆኑ ፡ በሁላችሁም ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ይህም ፡ ወዳጅነት ፡ በደስታ ፡ ዘመን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በመከራ ፡ ዘመንም ፡ ተፈትኖ ፡ ጥብቅ ፡ በሆነ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ የቆመ ፡ መሆኑን ፡ አሳይቷል ።

የዛሬ ፡ ፲፱ ፡ ዓመት ፡ ግፈኛው ፡ ጠላት ፡ አገራችንን ፡ በወረራት ፡ ጊዜ ፡ የሕዝባችንን ፡ አቤቱታ ፡ ለዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ለማቅረብና ፡ የኢትዮጵያንም ፡ ትግል ፡ ለመቀጠል ፡ ከውድ ፡ አገራችን ፡ ስንወጣ ፡ የስደት ፡ ዘመናችንን ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ለማሳለፍ ፡ ቈረጥን ።

በዚያም ፡ የመከራ ፡ ዘመን ፡ የእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ በተቻለን ፡ ሁሉ፡ እንድንጽናና ፡ ለማድረግ ፡ ይጥር ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ገልጸንላችኋል ። ኢትዮጵያን ፡ በግፍ ፡ የወረራት ፡ ጠላት፡ የግፍ ፡ ሥራውን፡ በመቀጠል ፡ የጋራ ፡ ጠላታችን ፡ በሆነን ፡ ጊዜ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችን ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ በመተባበር ፡ የፈጸመው ፡ ሥራ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ታሪክ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በዓለም ፡ ታሪክም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስፍራ ፡ ይዞ ፡ ይገኛል ።



ዛሬም ፡ የግርማዊት ፡ ዳግማዊት ፡ ንግሥት ፡ ኤልሳቤጥ ፡ እንግዳ ፡ ሆነን ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ በምንገኝበት፡ በአሁኑ፡ ጊዜ ፡ የእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ ለእኛና ፡ ለሕዝባችን ፡ ያለውን ፡ ፍቅር ፡ በጋለ ፡ አድናቆት ፡ በጕልህ ፡ አሳይቶናል ።

በየሄድንበት ፡ ሁሉ ፡ ሕዝቡ ፡ ልጅ ፡ ዐዋቂ ፡ ጌታ ፡ ድኻ ፡ ሳይለይ ፡ በአንድነት ፡ ደስታውን ፡ ፍቅሩን ፡ ገልጾልናል ። ይህም ፡ የተደረገልን ፡ የክብርና ፡ የወዳጅነት ፡ አቀባበል ፡ ለተወደደ፡ ሕዝባችን ፡ ጭምር ፡ የተደረገ ፡ መሆኑን ፡ ስለምናውቅ ፡ መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የደስታችን ፡ ተካፋይ ፡ እንደሚሆን ፡ እርግጠኛ ፡ ነን ።

አሁን ፡ የምናደርገው ፡ መጐብኘት ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ጥንታዊ ፡ ወዳጅነት ፡ በበለጠ ፡ አዲሷን ፡ እንዲያጠናው ፡ በኤኮኖሚና ፡ በትምህርት ፡ መስፋፋት ፡ ረገድ ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ እንዲስፋፋ ፡ ያለንን ፡ ተስፋ ፡ ስንገልጽላችሁ ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

# 444

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በአለፈው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ የዘመቱትን ፡ የእንግሊዝ ፡ መኰንኖች ፡ ከለብ፡ጥቅምት ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ረቡዕ ፡ ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ጐበኙ ። ማኅበሩም ፡ ስለ ፡ ግርማዊነታቸው፡ ክብር ፡ ባደረገው ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

የኢትዮጵያን ፡ ነፃነት ፡ ለማስመለስ ፡ በተደረገው ፡ ጦርነት ፡ የረዱትን ፡ የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ አባሎች፡ ከብዙ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለመገናኘት ፡ በመቻሌ ፡ ደስታዬ ፡ ልዩ ፡ ነው ።

ባለፈው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ጓደኞች፡ ከፈጸሙዋቸው ፡ የኅብረትና፡ የአንድነት ፡ ተግባሮች ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ተደረገው ፡ ጦርነት ፡ በስምምነትና፡ በጋለ፡ መንፈስ ፡ የተፈጸሙ፡ ዘመቻዎች፡ ያሉ ፡ አይመስለኝም ። ኃይሉን ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አጣምሮ ፡ ይሠራ ፡ የነበረው ፡ የጦር፡ ሠራዊታችን ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ጠላትን ፡ ከምሥራቃዊ ፡ አፍሪቃ ፡ አስወጥቶ ፡ በሰሜን ፡ አፍሪቃ ፡ ለተደረገው ፡ ጦርነት ፡ አስፈላጊው፡ ወታደርና፡ መሣሪያ፡ የሚተላለፍበትን፡ በር፡ ሊከፍት፡ ቻለ ።

የፈጸማችኋቸው ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ተግባሮች ፡ በኢትዮጵያና ፡ በእንግሊዝ ፡ ወዳጅነት ፡ ታትመው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራሉ ።

በሕይወት ፡ ላሉትና ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ለወደቁት ፡ የጦር ፡ መኰንኖች ፡ ክብር ፤ እንደዚሁም ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ላለው ፡ ጥንታዊ ፡ ወዳጅነት ፡ ጽዋዬን ፡ አነሣለሁ ።

# 445

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የእንግሊዝን ፡ አገር ፡ ጕብኝታቸውን ፡ ስለ ፡ ፈጸሙ ፡ ጥቅምት ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ረቡዕ ፡ ከማታው ፡ በ፰ ፡ ሰዓት ፡ የክብር ፡ ተከታዮቻቸውን ፡ አስከትለው ፡ ሎንዶን ፡ በቢክቶሪያ ፡ ጣቢያ ፡ ላይ ፡ በባቡር ፡ ተሳፍረው ፡ ወደ ፡ ዶበር ፡ ተጓዙ ። ዶበር ፡ ሲደርሱ ፡ ከባቡሩ ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ ተዛውረውና ፡ ሌሊቱን ፡ ባሕሩን ፡ ተሻግረው ፡ በልዩ ፡ ባቡር ፡ ወደ ፡ ፓሪስ ፡ ጕዞውን ፡ ቀጠሉ ። ጥቅምት ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ኀሙስ ፡ በ፭፡ ሰዓት፡ ፓሪስ ፡ ከተማ ፡ ደቡሎኝ ፡ ከሚባለው ፡ የባቡር ፡ ጣቢያ ፡ ደረሱ ። በጣቢያውም ፡ ላይ፡ የፈረንሳይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ሙሴ ፡ ረኔ፡ኰቴና ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሙሴ ፡ ማንዴስ ፡ ፍራንስ ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ተቀብለዋቸው ፤ ከፕሬዚዳንቱ ፡ ጋራ ፡ በግልጽ ፡ አውቶሞቢል ፡ ሆነውና ፡ በሰልፉ ፡ መካከል ፡ አልፈው ፡ ኤሊዜ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ገቡ ። በዚሁ ፡ ዕለት ፡ ማታ ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ስለ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ክብር ፡ በኤሊዜ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ታላቅ ፡ የእራት ፡ ግብዣ ፡ አደረጉ ።በግብዣውም ፡ ላይ ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

ሀ) የፕሬዚዳንቱ ፡ የሙሴ ፡ ረኔ ፡ ኰቴ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ይህ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ አጐበኛኘት ፡ ከአንድ ፡ ትውልድ ፡ የበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ሁለቱን አገሮቻችንን ፡ በወዳጅነት ፡ ያገናኘውን ፡ ጊዜ ፡ ለማስታወስ ፡ ምስክር ፡ በመሆኑ ፡ ዛሬ ፡ ለእኛ ፡ ክብራችን ፡ ነው ።

ከግርማዊነትዎ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ አጼ ፡ ምኒልክ ፡ ለአገራቸው ፡ እርምጃ ፡ መንገድ ፡ ይሠሩ ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ የዲፕሎማሲ ፡ ጕዳናና ፡ ዘመናዊ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ያቋቁሙ ፡ በነበረ ፡ ጊዜና ፡ እንዲሁም ፡ የትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ ሲመሠርቱና ፡ የምድር ፡ ባቡር፡መሥመሮችን ፡ ሲያሠሩ ፡ ለዚህ ፡ ከፍ ፡ ላለው ፡ ሥራ ፡ ተባብሮ ፡ ለመሥራት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡



የሚያሳስቡት ፡ የእኛን ፡ የአገሮቻችንን፡ ልጆች፡ ነበር ። የመጀመሪያው ፡ የፈረንሳይ ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ሙሴ ፡ ሉአንኮ ፡ ላጋርድ ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ወዳጆች ፡ መካከል ፡ አንደኛው ፡ ስለ፡ ነበሩ ፡ በ፲፱፻፲፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኤሊዜን፡ ቤተ፡ መንግሥት ፡ ለመጀመሪያ ፡ በጐበኙበት ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ፡ በላይ፡ የተጠቀሱትን ፡ መልክተኞችን ፡ በግልጽ ፡ ስላከበሯቸው ፡ በደስታ ፡ ልናስታውሰው ፡ ይገባናል ። እነዚህንም ፡ መታሰቢያዎች ፡ ስናነሣ ፡ ከኵራት ፡ ጋራ ፡ ነው ።

የግርማዊነትዎ ፡ ሁለተኛ ፡ አያትዎና ፡ ከንጉሥ ፡ ሉዊ ፡ ፊሊፕ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ የተሳሰረ ፡ ወዳጅነት ፡ የእምነት ፡ ምልክት ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ። ስለ ፡ ጋራ ፡ ማስረጃና ፡ በጠላት ፡ ኀይል ፡ ላይ ፡ ነፃነትን፡ ለማግኘት ፡ የደከምንበት ፡ የጋራ ፡ ድል ፡ እንደ፡ ገና ፡ ወዳጅነታችንን ፡ በበለጠ፡ ከማስተሳሰሩም ፡ በላይ ፡ በሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነትና ፡ ባለፉት ፡ ዓመታቶች ፡ ውስጥ ፡ ወዳጅነታችን ፡ እየጠነከረ ፡ ሄዷል ።

ወራሪን ፡ ለመከላከል ፡ ግርማዊነትዎና ፡ ሕዝብዎ ፡ በቈራጥነት ፡ ተቃዋሚ ፡ ለመሆኑ ፡ ዓለም፡ ከቶ፡ የሚረሳው፡ አይደለም ። ግርማዊነትዎ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወታደሮችዎ ፡ መሪ ፡ ሆነው ፡ በጐጃም ፡ በኩል ፡ በአሜድላ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ጦርነት፡ በጀመሩ ፡ ጊዜ ፤ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ወደ ፡ ዋና ፡ ከተማዎ፡ ለመግባት ፡ ቍርጠኛ ፡ እንደ፡ ነበሩ፡ አስታውሳለሁ ። የነፃ ፡ ፈረንሳይ ፡ ወታደሮች ፡ በማግሥቱ ፡ የሚገኘውን ፡ የሰላም ፡ ወዳጅ ፡ ለመርዳት ፡ ከከረንና ፡ ከኩብኩብ ፡ ከሌሎቹ ፡ ወታደሮች ፡ ጐን ፡ ተሰልፈው ፡ ያደረጉትን ፡ ውጊያ ፡ ለማስታወስ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ እንዲፈቅድልኝ ፡ እለምናለሁ ።

በተገኘው ፡ የሰላም ፡ ጊዜም ፡ ውስጥ ፡ ጎረቤት ፡ የሆነችው ፡ ወዳጃችን ፡ ከመለያየት ፡ በመካፈል ፡ በተደረገው ፡ የወሰን ፡ ክልል ፡ አመሠራረት ፡ ሊረጋገጥ ፡ ተችሏል ። የተወዳጅ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ የፈረንሳይንና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሊሴ ፡ ስለ ፡ መሠረተ ፡ ያለ ፡ ጥርጥር ፡ የአስደናቂነትዎ ፡ ማስረጃ ፡ በፈረንሳዮች ፡ ሁሉ ፡ ሊታወቅ ፡ ተችሏል ።

ግርማዊ፡ሆይ፡ ይህ፡በፈቃድዎ፡ ያደረጉት፡ጕብኝት ፡ ለወዳጅነታችን ፡ ምስክር ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ለአሁን ፡ ፍሬ ፡ ለተመላበት ፡ ተስፋ ፡ እኛ ፡

በበለጠ ፡ እንደ ፡ ውድ ፡ የምንፈቅደው ፡ ነው ። በግርማዊነትዎ ፡ ረዳትነት ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሴቶች ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሊሴ ፡ ለመሥራት ፡ ያለኝን ፡ ምኞት ፡ እገልጻለሁ ። በአገርዎ ፡ ውስጥ ፡ በሲያንቲፊክ ፡ ረገድ ፡ ለመስፋፋት ፡ የቀረበው ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ጥያቄ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ላይ ፡ ተቋቁሞ ፡ የሚገኘውን ፡ እንስቲትዊ ፡ ፓስተር ፡ ለማስረጃ ፡ ያህል ፡ መጥቀስ ፡ በቂ ፡ ነው ። የአርኬኦሎጅ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ፈቃድ ፡ ለፈረንሳይ ፡ ሊቆች ፡ በተሰጠ ፡ ጊዜ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የሥራው ፡ ውጤት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለመግለጽ ፡ ችሏል ። የፈረንሳይና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዋናው ፡ የወዳጅነት ፡ ምልክት ፡ አመሠራረት ፡ የግርማዊነትዎ ንና ፡ የሕዝብዎን ፡ የጀግንነት ፡ ታሪክ ፡ ከማጕልመሱም ፡ በላይ ፡ ለጋራ ፡ ክርስቲያንነታችን ፡ መሠረትና ፡ ለሥልጣኔያችን ፡ እድገት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስክር ፡ ነው ።

ጅቡቲ ፡ ግዛታችንና ፡ አገርዎን ፡ የሚያገናኟቸው ፡ ጥቅሞች ፡ ጥበባችንን ፡ ለማደርጀት ፡ የሚረዳ ፡ ነው ። ታማኝ ፡ የሆነውን ፡ መልክ ፡ የያዘው ፡ የፈረንሳይና ፡ የኢትዮጵያ ፡ የምድር ፡ ባቡር ፡ የፖለቲካችንንና ፡ የኤኮኖሚያችንን ፡ ጥንካሬ ፡ ዕጥፍ ፡ እያደረገው ፡ ሄዷል ። ለወደፊት ፡ በሙሉ ፡ አፍሪካ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ተባብሮ ፡ ለመሥራትና ፡ ለያንዳንዱ ፡ ለሚሆነው ፡ ድርጅት ፡ ቢሆንም ፡ ባይሆንም ፡ ለነገው ፡ ዓለም ፡ ደስታ ፡ የሚሆነውን ፡ ማከናወን ፡ የሚገባቸው ፡ ሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ ናቸው ። ለዚህ ፡ ለፖለቲካ ፡ ለወዳጅነት ፡ የተረጋገጠ ፡ ዋስትናና ፡ ኗሪ ፡ ምልክት ፡ መሆኑን ፡ ግርማዊነትዎ ፡ እንደሚገምቱት ፡ በአንድ ፡ ቃል ፡ ተስማምተናል ።

ለግርማዊነትዎ ፡ ክብር ፡ እንዲሁም ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ጤና ፡ በመመኘትና ፡ እንዲሁም ፡ ለልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍን ፡ ሐረር ፡ ክብር ፡ ጽዋዬን ፡ ሳነሣ ፡ በፈረንሳይ ፡ አንድነትና ፡ ሬፑብሊክ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ የማቀርበው ፡ ምስጋና ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ መሆኑን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ስገልጽ ፡ እንዲሁም ፡ በሙሉ ፡ ለሕዝብዎና ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብዎ ፡ መልካም ፡ ጤና ፡ እየተመኘሁ ፡ ነው ።

* * *



ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ ፕሬዚዳንት ፤

ክብርት ፡ ፕሬዚዳንቲቱ ፤

የተከበራችሁ ፡ መኳንንት ፤

ክቡር ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ባቀረቡልኝ ፡ ጥልቅ ፡ ቃል ፡ ደስ ፡ ስላለኝ ፡ አመሰግንዎታለሁ ። ይህም ፡ ቃል ፡ ሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ በወዳጅነት ፡ መተሳሰራቸውን ፡ የሚገልጽ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ እንዳንድ ፡ ዐይነተኛ ፡ ምስክር ፡ አድርጌ ፡ እቀበለዋለሁ ። ዛሬ ፡ ፈረንሳይ ፡ በመካከለኛው ፡ ምሥራቅና ፡ በተለይም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ የታሪክ ፡ ዐምድ ፡ ይዛ ፡ ትገኛለች ። ጥበባችሁና ፡ ያገር ፡ ወግና ፡ ልማዳችሁ ፡ መሠረት ፡ የማይለቅ ፡ ሆኖ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ይገኛል ፡ የሚባል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በሌሎችም ፡ የኤውሮፓ ፡ አገሮችም ፡ እንዳለው ፡ ሁሉ ፡ ኢትዮጵያም ፡ በመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ የክርስቲያን ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ አንዷቱ ፡ ታላቅ ፡ አገር ፡ ናት ። ይኸውም ፡ ማነኛውንም ፡ የክርስቲያን ፡ ባህል ፡ እንዲሁም ፡ ወግና ፡ ልማዱን ፡ አቀናብራ ፡ የያዘች ፡ ታላቅ ፡ አገር ፡ ናት ። አሁን ፡ ክቡርነትዎ ፡ ፈቃዱ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ጠቀሰው ፡ ሁሉ ፡ በ፲፰፻፺፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በቅድም ፡ አያቴና ፡ በንጉሥ ፡ ሉዊ ፡ ፊሊፕ ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ስምምነት ፡ ከዘመናዊው ፡ የመንግሥታት ፡ መግባባት ፡ መካከል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከዚህ ፡ ታላቅ ፡ አገር ፡ ጋራ ፡ ያደረገችው ፡ ስምምነት ፡ የመጀመሪያ ፡ ጊዜዋ ፡ ነው ። ይህም ፡ ረጅም ፡ የሆነው ፡ የወዳጅነትና ፡ የመግባባት ፡ ወግና ፡ ልማድ ፤ በሙሉ ፡ ከሚቈጠሩ ፡ ዘመናት ፡ ጀምሮ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ከዚህ ፡ ከታላቅ ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ ሊያወዳጀው ፡ ዐይነተኛ ፡ ምክንያቱ ፡ ሆኗል ።

በ፲፱ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ መልክተኛ ፡ ሆነው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ አውሮፓውያኖች ፡ እጅግ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ የነበሩትንና ፡ በጣም ፡ የታወቁትን ፡ የፈረንሳይ ፡ መንግሥት ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ እንደራሴ ፡ ሙሴ ፡ ላጋርድን ፡ የተወዳደራቸው ፡ ከቶ ፡ ማንም ፡ የለም ። እሳቸው ፡ ያገራቸውን ፡ መብት ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲያገለግሉ ፡ እንዲሁም ፡ የኢትዮጵያን ፡ መብት ፡ ለመጠበቅ ፡ ጠንቅቀው ፡

ያውቁ ፡ ነበሩ ። ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ የፈረንሳይ ፡ ጥበብና ፡ ዝናዋ ፡ በኢትዮጵያ ፡ እየተስፋፋ ፡ የሄደው ፡ ከዚያ ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

ይህም ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ መግባባትና፡የመረዳዳት ፡ መጠን ፡ ከዓመት ፡ ወደ ፡ ዓመት ፡ እየተሸጋገረ ፡ በተለይም ፡ ስለ ፡ ጥበብ ፡ ተባብሮ ፡ መሥራት ፡ ላለው ፡ ጥረት ፤ ለኤኮኖሚና ፡ ለሌሎቹም ፡ ክቡርነትዎ ፡ ለጠቀሰው ፡ይህንን ፡ ለመሳሰሉ ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ ዐይነተኛ ፡ ግምት ፡ የሚሰጥ ፡ ሆኖዋል ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ልዩ ፡ መደሰት ፡ የሚያቀርበው ፡ የመረዳዳቱ ፡ ሥራ ፡ እየተስፋፋ ፡ መሄዱን ፡ በማሳየቱ ፡ ነው ።

እጅግ ፡ ከፍ ፡ ላለው ፡ ወግና ፡ ልማድዋ ፡ እንዲሁም ፡ ለዐይነተኛው፡ የጥበብ ፡ አገልግሎቷ ፡ አሳብ ፡ ታማኝነት ፡ ያላት ፡ ፈረንሳይ ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ያሳየችው ፡ ሥልጣኔ ፡ ስምዋን ፡ ከፍ ፡ እንዳደረገው ፡ መጠን ፡ በኢትዮጵያም ፡ ባሳየችው ፡ ሥራ ፡ ከመደሰት ፡ አታቋርጥም ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ጥንታዊ ፡ የሆነው ፡ ወዳጅነት ፡ መሠረቱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ በወደቁት ፡ ጀግኖቻችሁ፡ ደም ፡ የታተመ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፤ ይህ ፡ የፈሰሰው ፡ ደም ፡ ስለ ፡ ሴኩሪቲ ፡ ኮሌክቲብ ፡ መከላከል ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ የዓለምን ፡ ሰላም ፡ ለመጠበቅ ፡ የሚችል ፡ ይኸው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

አሁን ፡ ስለ ፡ ክቡር ፡ ፕሬዚዳንትና ፡ ስለ ፡ ክብርት ፡ ባለቤትዎ ፡ ደግሞም ፡ ለታላቁ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወዳጅ ፡ ስለሆነው ፡ የፈረንሳይ ፡ ሕዝብ ፡ ጤና ፡ ጽዋዬን ፡ አነሣለሁ ።

# 446

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጥቅምት ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ማታ ፡ ስለ ፡ ክቡር ፡ የፈረንሳይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ክብር ፡ ፓሪስ ፡ ባለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኤምባሲያቸው ፡ ባደረጉት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ።

ክቡር ፡ ፕሬዚዳንት ፤

እመቤቶችና ፡ ጌቶች ፤

ልክ ፡ የዛሬ ፡ አምሳ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ የተወደዱ ፡ አባታችን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የመጀመሪያ ፡ መልክተኛ ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡



ፓሪስ ፡ መጥተው ፡ ነበር ። እሳቸውም ፡ መልካም ፡ ስሜቶች ፡ ይዘው ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ እኛም ፡ ከዚሁ ፡ መንገዳቸው ፡ ደስ ፡ የሚያሰኙ ፡ መታሰቢያዎች ፡ አስቀርተን ፡ ነበር ። ልክ ፡ የዛሬ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ደግሞ ፡ ራሳችን ፡ የፕሬዚዳን ፡ ሚሌራን ፡ እንግዳ ፡ ሆነን ፡ ወደ፡ፈረንሳይ ፡ አገር ፡ መጣን ፤ ይህም ፡ መጐብኘት ፡ ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ ጀምሮ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ጸንተው ፡ የቈዩትን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኙ ፡ ግንኙነቶች ፡ በበለጠ ፡ ለማጠንከር ፡ አገልግሏል ፡ ብለን ፡ ለማመን ፡ እንፈልጋለን ።

ከስድስት ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ የንግሥ ፡ በዓላችን ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ ፈረንሳይ ፡ መልካም ፡ ፈቃዷ ፡ ሆኖ ፡ የታወቁትን ፡ ማሬሻል ፡ ፍራንሼ ፡ ዴስፔሬን ፡ ልካቸው ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ይህ ፡ አሁን ፡ የምናደርገው ፡ መጐብኘት ፡ በኢትዮጵያና ፡ በፈረንሳይ ፡ መካከል ፡ ጸንተው፡የቈዩትን ፡ ግንኙነቶች ፡ ከፍተኛነት፡የሚገልጽ ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ምስክርነት ፡ ከመሆኑ ፡ በተቀር ፡ ለታወቀውም ፡ ለፈረንሳይ ፡ የእንግዳ ፡ ተቀባይነት፡ሞያ፡አንድ ፡ አዲስ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ።

በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ከተደረገልን ፡ የወዳጅነት ፡ መልካም ፡ አቀባበል ፡ በኋላ ፡ በበኩላችን ፡ ደግሞ ፡ ለሚያስተሳስረን ፡ የጥቅምና ፡ የሐሳብ ፡ አንድነት ፡ ልዩ ፡ መግለጫ ፡ እንዲሆን ፡ የታላቋን ፡ የፈረንሳይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ በፓሪስ ፡ ከተማ ፡ በሚገኘው ፡ በኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ በእንግድነት ፡ ስንቀበላቸው ፡ የተለየ ፡ ደስታ ፡ ይሰማናል ።

ለክቡር ፡ የፈረንሳይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ጤናና ፡ ወዳጅ ፡ ለሆነች ፡ ለዚች ፡ ታላቅ ፡ አገር ፡ ልማትና ፡ ደኅንነት ፡ ጽዋችንን ፡ እናነሣለን ።

# 447

ጥቅምት ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ማታ ፡ የፈረንሳይ፡መንግሥት ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር ፡ ስለ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ክብር ፡ በውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ ባደረጉት ፡ የእራት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ንግግር ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ክቡር ፡ ሚኒስትር ፤ እመቤቶች ፡ ጌቶች ፤

በኢትዮጵያና ፡ በፈረንሳይ ፡ መካከል ፡ የተዘረጉት ፡ ዲፕሎማቲካዊ ፡

ግንኙነቶች ፡ የተጀመሩበት ፡ ዘመን ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ እጅግ ፡ የራቀ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ገና ፡ በ፲፮ኛ ፡ እምስተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ ንጉሥ ፡ ቀዳማዊ ፡ ይስሐቅ ፡ ከፈረንሳይ ፡ ንጉሥ ፡ ከስድስተኛው ፡ ሻርል ፡ ጋራ ፡ በጽሕፈት ፡ ግንኙነት ፡ ነበረው ። በዐሥራ ፡ ሰባተኛውና ፡ በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ክፍለ፡ዘመናት ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ቻይናና ፡ እንደ ፡ ጃፓን ፡ የገለልተኝነትን ፡ ፖሊቲካ ፡ ተከትላ ፡ ነበር ። ይሁንና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ካንድ ፡ ኤውሮጳዊ ፡ አገር ፡ ጋራ ፡ በመጀመሪያ ፡ የተፈራረመችው ፡ ውል ፡ በ፲፰፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሉዊ ፡ ፊሊፕ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የተከናወነው ፡ ነበር።ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ፈረንሳይ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያላት ፡ ክብር ፡ እያደገ ፡ ከመሄድ ፡ አላቋረጠም ። በዐሥራ ፡ ዘጠነኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዘንድ ፡ ተወክለው ፡ ከነበሩት ፡ የኤውሮጳ ፡ መንግሥታት ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ እንደራሴዎች ፡ መካከል ፡ በስመ ፡ ጥሩነታቸው ፡ የታወቁትን ፡ የፈረንሳይ ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ እንደራሴ ፡ ሙሴ ፡ ላጋርድን ፡ ለመወዳደር ፡ የሚመኝ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ አልነበረም ። እኒህ ፡ ሰው ፡ ላገራቸው ፡ ጥቅም ፡ መሥራትን ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ለኢትዮጵያም ፡ ጥቅም ፡ መሥራትንም ፡ ዐውቀው ፡ ነበር ።

አሁን ፡ ባለንበት ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ በመጀመሪያዎቹ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ከፈረንሳይ ፡ ጋራ ፡ የተፈረመው ፡ የክሎቡኮቭስኪ ፡ ውል ፡ ከመጨረሻው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ በፊት ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሌሎቹ ፡ የውጭ ፡ መንግሥታት ፡ መካከል ፡ የተፈረሙት ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡ ዐይነተኛ ፡ መሠረት ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ በስተቀር ፡ በሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ መጨረሻ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ብለው ፡ ይታዩ ፡ የነበሩት ፡ ጕዳዮች ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ የደረሱት ፡ ፓሪስ ፡ በተደረገው ፡ የሰላም ፡ ጉባኤ ፡ መሆኑን ፡ እናስታውሳለን ።

ስለዚህ ፡ ሁለቱን ፡ አገሮች ፡ አስተሳስረዋቸው ፡ የሚገኙት ፡ ከአራት፡ መቶ ፡ ዘመናት ፡ በሚበልጥ ፡ ረጅም ፡ የግንኙነት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የተመሠረቱት ፡ ባህሎችና ፡ መታሰቢያዎች ፡ ናቸው ። በዓለም ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ እንደሚደርሰው ፡ ሁሉ ፡ የግንኙነታችንን ፡ ታሪክ ፡ አንዳንድ ፡ አስቸጋሪ ፡ የሆኑ ፡ ጕዳዮች ፡ ሳይገጥሙት ፡ አልቀረም ።



ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህን ፡ ጕዳዮች ፡ ዘወትር ፡ የሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ጥቅም ፡ ባልተበደለበት ፡ መንገድ ፡ ለመፈጸም ፡ ተችሎአል ።

በጥልቅ ፡ ወዳጅነት የተሳሰሩት ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ የተመሠረቱት ፡ እነዚህ ፡ ግንኙነቶች ፡ እያደጉ ፡ እንዲሄዱ ፡ ጽዋችንን ፡ እናነሣለን ።

---

# 448

የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሐያ ፡ አራተኛ ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፭ ፡ ሰዓት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በፓርላሜንቱ፡ሲከበር፤ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ክቡር ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ስም ፡ ለፓርላሜንቱ ፡ ያቀረቡት ፡ የዙፋን ፡ ቃል ።

ሀ) ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በፓርላሜንቱ ፡ ውስጥ ፡ የተናገሩት ፡ የመግለጫ ፡ ንግግር ።

የተከበራችሁ ፡ መማክርት ፤

ሁላችሁም ፡ እንደምታውቁት ፡ ታላቁ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የወዳጆች ፡ መንግሥቶችን ፡ ግብዣ ፡ በመቀበል ፡ በአውሮፓ ፡ በሚገኙበት ፡ ጊዜ ፤ አጋጣሚ ፡ ሆኖ ፡ የግርማዊነታቸው ፡ የዘውድና ፡ የፓርላማው ፡ መከፈት ፡ በዓል ፡ ግርማዊነታቸው ፡ በመናገሻ፡ከተማቸው ፡ በሌሉበት ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ዋለ ፡ ፓርላማው ፡ እንዲከፈትና ፡ ሥራውን ፡ እንዲጀምር ፡ ለፓርላማው ፡ እንዳደርስ ፡ በተለይ ፡ የታዘዘኩትን ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ መልእክት ፡ በተከበራችሁ ፡ መማክርት ፡ ፊት ፡ ተገኝቼ ፡ አነባለሁ ።

ዛሬ ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትን ፡ መልእክት ፡ ለእናንተ ፡ ለማድረስ ፡ በተሰጠኝ ፡ ዕድልና፡ክብር ፡ ደስ ፡ እያለኝ ፡ ለተወደዱ ፡ አገራቸውና ፡ ሕዝባቸው ፡ ክብርና ፡ ገናናነት ፡ በታሪክ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሲነገር ፡ የሚኖረው ፡ ይህ ፡ መጐብኘት ፡ በመልካም ፡ ተፈጽሞ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በግርማዊነታቸው ፡ ዙሪያ ፡ እንድንገኝ ፡ የምመኘውን ፡ ምኞት ፡ በበኩሌ ፡ እገልጻለሁ ።

ለ) ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ያነበቡት ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የዙፋን ፡ ቃል ።

በያመቱ ፡ አደራችንን ፡ እየሰጠን ፡ ወደ ፡ ዓመት ፡ ሥራው ፡ እንዲገባ ፡ የምንከፍተው ፡ ፓርላማችን ፡ ያመት ፡ ሥራውን ፡ ለመጀመር ፡ በተ

ሰበሰበበት ፡ ቀን ፡ ለመገኘት ፡ ያልቻልነው ፡ ዛሬ ፡ ብቻ ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

በዚህም ፡ ቀን ፡ የወዳጆችን ፡ ነገሥታትና ፡ ፕሬዚዳን ፡ ጥሪ ፡ ተቀብለን ፡ በአውሮፓ ፡ እንገኛለን ። ባለፉት ፡ ወራቶች ፡ በወዳጆች ፡ አገሮች ፡ ጥሪ ፡ ዩናይትድ ፡ ስቴት ፡ ኦፍ ፡ አሜሪካን ፡ ካናዳን ፡ ሜክሲኮን ፡ ዩጎስላቪያን ፡ ግሪክን ፡ ለመጐብኘት ፡ ሄደን ፡ እንደ፡ነበረ ፡ ዛሬም፡በአውሮፓ ፡ የምንገኝበት ፡ መጐብኘት ፡ ኢትዮጵያን ፡ አገራችንንና ፡ የተወደደ ፡ ሕዝባችንንም ፡ ታሪክ ፡ ከፍ ፡ የሚያደርግ ፡ ደግሞ ፡ ከወዳጆች ፡ አገሮችና ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ የሚገኘውን ፡ መልካም ፡ መገናኛ ፡ የሚያጸና ፤ በፖለቲካና ፡ በኤኮኖሚም ፡ የሚያሳድግ ፡ ፍሬ ፡ የሚገኝበት ፡ እንዲሆን ፡ የምናምንበት ፡ ነው ።

ባለፈውም ፡ መንገዳችን ፡ በዛሬውም ፡ የተደረጉልን ፡ የልብ ፡ የወዳጅነት ፡ አቀባበል ፡ ማረጋገጫ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

ይህ ፡ መልእክታችን ፡ እንዲደርሳችሁ ፡ ስናደርግ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ በፊታችሁ ፡ ለተደቀነው ፡ ሥራ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምታድግበትን ፡ የተወደደ ፡ ሕዝባችን ፡ የሚጠቀምበትን ፡ ለመፈጸም ፡ እንድትችሉ ፡ በሥራችሁ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መሪ ፡ መንፈስ ፡ እንዲያድርበት ፡ እንመኝላችኋለን ።

## 449

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ጕብኝታቸውን ፡ ስለ ፡ ፈጸሙ ፡ የክብር ፡ ተከታዮቻቸውን ፡ አስከትለው ፡ ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ማክሰኞ ፡ ማታ ፡ በልዩ ፡ ባቡር ፡ ከፓሪስ ፡ ወደ ፡ ሆላንድ ፡ ተጓዙ ።

ጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ረቡዕ ፡ ከጧቱ ፡ በ፬ ፡ ሰዓት ፡ አምስተርዳም ፡ ከተማ ፡ ደረሱ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ጁሊያናና ፡ ባለቤታቸው ፡ ፕረንስ ፡ ቤርናንድ ፡ በባቡር ፡ ጣቢያ፡ በታላቅ፡ ክብር ፡ ተቀብለዋቸው ፡ ወደ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ፡ሄዱ ። በዚሁ ፡ ዕለት ፡ ማታ ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ጁሊያና ፡ ስለ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ክብር ፡ ታላቅ ፡ የራት፡ ግብዣ፡ አደረጉ። በግብዣውም ፡ ላይ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ጁሊያና ፡ ላደረጉት ፡ ንግግር ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠው ፡ መልስ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።



ግርማዊት ፡ ሆይ ፤

ልዑል ፡ ሆይ ፤

ክቡር ፡ ሆይ ፤

ስለኔና ፡ ስለ፡ ሕዝቤ ፡ ለተናገሩዋቸው፡ መልካም ፡ ቃሎችና ፡ እንደዚሁም ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሆላንድ ፡ መካከል፡ ስላለው ፡ የረጅም ፡ ዘመን ፡ ግንኙነት ፡ በተሳካ ፡ አነጋገር ፡ ዘርዝረው፡ ስለ፡ ገለጡት፡ ታሪክ ፡ ከልብ ፡ አመሰግንዎታለሁ ።

ክቡርነትዎ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ብርታትና ፡ ትጋት ፡ አመስግነው ፡ ተናግረውታል ። ነገር ፡ ግን ፡ በየጊዜው ፡ ለነፃነቱ ፡ በመከላከል ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ አእምሮና ፡ እጅ ፡ በሚሠሩ ፡ ሥራዎችና ፡ በማዕበል ፡ አደጋ ፡ ከሚደርሱ ፡ ጉዳቶች ፡ ለመዳን ፡ በጥንካሬና ፡ በቈራጥነት ፡ በመሥራት ፡ እንደ ፡ ሆላንድ ፡ ሕዝብ ፡ በዓለም ፡ የሚመሰገኑና ፡ የሚደነቁ ፡ ጥቂት ፡ አገሮች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

ደግሞ ፡ ክቡርነትዎ ፡ በንግግርዎ ፡ የገለጡት ፡ የሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ግንኙነት ፡ ታሪክ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ጠቅላላ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ የሚቈጠር ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ሁለቱ ፡ አገሮች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ ተቃርበውና ፡ ተባብረው ፡ ለመሥራት፡ የሚችሉበት ፡ መሠረት ፡ ሆኖዋቸዋል ፤ ዛሬም ፡ የሆላንድ ፡ ካፒታል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ እንዱስትሪ ፡ በማቋቋም ፡ የመሐንዲስነትንና ፡ የእርሻ፡ ሥራዎችን ፡ በመሥራት ፡ ለአገራችን ፡ ልማትና ፡ ለኤኮኖሚያችን ፡ ስፋት ፡ ላቀድነው ፡ ፕሮግራም ፡ ረድቷል ፤ ወደፊትም ፡ የሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መረዳዳት ፡ እየቀጠለ ፡ ለመሄድ ፡ የሚቻል ፡ መሆኑን ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ባደረግሁት ፡ መጐብኘት ፡ ተረድቻለሁ ፤ ሁለቱ ፡ ሕዝቦቻችን ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ በሰፊው ፡ እንደሚረዳዱና ፡ ጥልቅ ፡ ወዳጅነታቸውም ፡ እየደረጀ ፡ እንዲሄድ ፡ አምናለሁ ።